Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto
ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ
E-mail: torontofinote@gmail.com

# አለማረፍ የተርብ ቤት መቆስቆስ

## የ ፍኖተ ሳተላይት ሬድዩ ሐተታ (የካቲት 2 2015)

ለህዝብ ሀይማኖት ብዙውን ጊዜ የህልውና ጥያቄ ነው፡፡ የሞት ሽረት ጉዳይ፡፡ አላርፍ ያለው ኮለኔል ቆሻሻ መዳፉን ሃይማኖት ላይ ሊያሳርፍ ፣ሊጭን ተነስቷል፡፡ አለማረፍ የተርብ ቤት መቆስቆስ፡፡ ተዋህዶ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ማንነት ገላጭ ሀይማኖት ነው፡፡ ይህን ያልተረዳው መሃይም ኮለኔል በብሄሩ መሰረት ቄሮአዊ ቄስን የኦሮሞ ጳጳስ ብሎ በህገ ወጥ አሹሞ ሲኖዶሱን ለማፍረስና በየብሄሩ ለመበታተን አድብቶ ተነስቷል፡፡ ክልል የሚለውንም እያበዛ እያስበዛ ነው፡፡ በሲኖዶሱ ላይ ለተቃጣው ጸያፍ ሴራ አገዛዙ ያለበትና የተጨማለቀበት እንጂ የጥቂቶች የዘፈቀደ እርምጃ አይደለም፡፡ ውጉዝ ከመ አርዮሱ ኮለኔሉንና ዘረኛውን አገዛዝ ይመለከታል፡፡ ህዝብ በየቦታው በተቃውሞ መነሳቱ የሚጠበቅና መሆንም ያለበት ነው፡፡ ተቃውሞን በአፈና አስቆማለሁ የሚለው የአገዛዙ ድንፋታም በራሱ ላይ ከፍተኛ መዘዝን ከማትረፍ ውጭ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ በዚህ ተቃውሞ የሌሎች ሃይማኖት መሪዎችና ምዕመናን ተካፋይ እንዲሆኑም ይጠበቃል፡፡

ጳረ ሲኖዶሱ ሰይጣናዊ እርምጃ በሂደቱ ጎን ሁለት ጠቃሚ ማጋለጦችን ፍንትው አድርጎ አሳይቶናል፡፡ ለማመን የሚያስቸግር፤ የሚያሳፍርም! ቢሆንም አሁንም ድረስ፤ ስውዩው ማንነቱን በደም አጨማልቆ ይኸው እዩት ብሎን ካበቃም በኋላ ኮለኔሉ በወንጀልና በጳረ ተዋህዶ ድርጊቱ የለበትም የሚሉን ስላሉ፤ ይህ የገሃድ ጳረ ተዋህዶ ሲኖዶስ ድርጊቱ ለአንዴም ለሁሊም ያጋልጠዋል፡፡ ኮለኔሉ አምባገነን ነው ፡፡ በሂደት እንደ መንግስቱም እንደ መለስም ፍጹም አምባገነን ለመሆንም ምኞት አለው፤ እየጣረም ነው፡፡ እስካሁን አልቻለበትም እንጂ ኢትዮጵያን ማሽመድመድ፤ መከፋፈል፤ በኦሮሚያ መተካትም ፍላጎቱ ነው፡፡ ከእሱ ወደ ቀኝ የከረሩና አላጠግብ ያላቸው የሚያወግዙት ዘረኞች ይኖራሉ፤ አሉም፡፡ ግን የእሱን ዘረኝነት የሚሰርዙ አይደሉም፤ አልሆኑም፡፡ አገዛዙ ብሄርተኛና ጠባብ ነው _የኦነግ ተቀጥላ፡፡ የብልጽግና ልፈፋ ተጨፈኑ ላሞኛችሁ እንጂ ምንም ሌላ ትርጉም ዋጋ፤ ሚዛን ያለው አይደለም፡፡ በውስጣቸው ውዝግብና ጉንተላ እየደራ ቢመጣም ስልጣን በኮለኔሉ እጅ ውስጥ ናት፡፡ ገድሎ አላውቀውምን ከመንግስቱ ቢወርስም አለእሱ ፈቃድ የሚወሰድ ምንም ዋና እርምጃ የለም፡፡ ይህ ዛሬም ተረጋግጧል፤ ጳረ ሲኖዶሱ እርምጃ ግልጽ አድርጎታል፡፡ በዚህም ብዙሃኑ ምን ያህል ኮለኔሉን ሆነ አገዛዙን እንደሚጠላም ታይቷል ፡፡ ሙሴ፤ ሙሶሊኒ መሆኑም ታውቋል፡፡ ሥልጣኑ እየተናደ ነው ብንልና መፈንቅል ሳይቀር እያንጃበበት ነው ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ የለውጥ መፈክርም እየጮኸበት ነው፤_ መሰረታዊ ለውጥ፡፡ ጳረ ሲኖዶሱን የዲያብሎስ እርምጃውን አንደምታ ሊያቀል ሆነ በሀሰት ክርክር ተገቢና ትክክል ለማድረግ ለማስመሰል ያደርገውን ሙከራ ሲኖዶሱ ራሱ ያጋለጠውና ውሸት ያለው ሲሆን በድርጊቱ አጁ እንዳለበት ከማሳየት ውጪ ተቃውሞውን አልቀነሰለትም፡፡ ነገ ደም ማፍሰሱ ስለማይቀር ይህም ከይሲ ዘረኛ እርምጃው ከመጪ ውድቀቱ የሚያድነው አይሆንም ፡፡

ሁለተኛው ግልጽ ሆኖ የመጣው ጉዳይ ደግሞ የቀበሮ ባህታውያንን ይመለከታል፡፡ ብዙሃኑ ኮለኔሉን ዓይንህን ላፈር እንዳለውና እንደጠላውም ሁሉ እስከ ትላንት ህዝብን ክደው ለዘረኛው አገዛዝ ተጎንብሰው ቆይተው የነበሩትም፤ ህዝብ ከሞላ ጎደል ወግዱ

ብሏቸው ከመድረክ ተገልለው የነበሩት ጉዶች አመቺ ጊዜና ዕድል አገኘን ብለው አንገታቸውን አቅንተዋል፡፡ ለህዝብ ሃይማኖት ተቆርቋሪ መስለው፤ ጸረ ሲኖዶሱን ሰይጣናዊ እርምጃ የሚቃወሙ መስለው ወደ መድረክ ብቅ እያሉም ነው። የህዝብን ትግል እንደገና ፈር ሊያሳጡ፤ ከሃዲድ ሊያወጡ፤ ለዘረኛ አገዛዝ ሊጠቅሙ እንጂ ሌላ ግብ የላቸውም፡፡ ዓላማቸው ማንንም ግራ የሚያጋባ ሊሆን የሚችልም አይደለም ፡፡ አንዴ ስላወናበዱ ሁሌም በጠራራ ጸሃይ የሚሸውዱን መስሏቸው ቢወራጩም አይሳካላቸውም፡፡ አማኙን ስናውቀው፤ ማን መናፍቁን ከሰልፍ ደባለቀው የሚያሰኝ ነው፡፡ የኮለኔሉን ድርጊቱን ያወገዙ መስለው ህዝብ ጎራ ተደባልቀው የህዝብን ትግል ለማኮላሸት ነው፡፡ እነማን ብሎ የሚጠይቅ ይኖራል ብለን አንጠብቅም፡፡ ከአገዛዝ አገዛዝ እንደ ፌንጣ ሲዘሉ በትዝብት አይተናቸዋል፡፡ ሀገር ወዳዱ ሲፈጅ የፍየል ምላሳቸው ዝምታን ሲያቅፍም ጉድ ብለን ቆይተናል፡፡ ለኮለኔሉ ትላንትም ጥብቅና ሲቆሙለት ነበር፡፡ ካህናት ሲታረዱ፤ቤተ ክርስቲያናት ሲጋዩና ታሪካዊ ቅርሶች ሲቃጠሉ ወንጀለኛውን ሙሴ ብለው አቅፈው ሲቀጥሉም በዓይናችን አይተናል፤በጆሮአችን ሰምተናቸዋል፡፡ ህዝብ ጎራ ሊገቡ ፍቃድ የሚያገኙ ሊሆኑ አይገባም።

ጸረ ሲኖዶሱ እርምጃ ፖለቲካዊም ሀይማኖታዊም ማጠየቂያ አለው፡፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፤የህዝብ አንድነት አንዱ መግለጫ የሆነውን ሀይማኖት ማፍረስ ማዳከም የዘረኛ ትልማቸው ወሳኝ እቅድ ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማን ከማርከስ እርምጃቸው ጋር ተያይዞ የሚፈረጅም ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኮለኔሉ ሀይማኖት መስራቾችና አቀንቃኞቹ ባዕዳን የተዋህዶን መጥፋት እንደ ዋሃቢስቶቹ አጥብቀው ይፈልጉታል ፡፡ የኮለኔሉ እገዛዝ ከመጣ ጀምሮ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተጎዳች እንጂ ቅንጣትም ያገኘችው ጥቅም የለም፡፡ ኮለኔሉ ዓይኑን በጨው አጥቦ ዋሽቷል፡፡ እንደ ሁሌም፡፡

በጋራና ቆራጥ ትግል ዘረኛውንና ዲያብሎሱን አገዛዝ እናውድም !!

ድል ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት !!